# አንድ ቁጥር….

ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጉዞአችን ጀምርን። ወደ ፍቅር ከተማ ወደ ሆነችው ድሬደዋ። ድሬደዋ ጉዞአችን መነሻ የሆነው ወርቃማ የሆነ ዕድል ተገን አድርገን ነው። መኪና ውስጥ ያለው ካሜራ ማን እንቅልፍ ቢጫነውም ወደ ፀሀይ መውጫ የምናደርገው ጉዞ አስደሳች እንደሚሆን ተስፋ አደረግን። የፀሀይ ወጋገኑ ይበልጥ እያጎላ ሲመጣ ደግሞ ተስፋችንን እውነት መሆኑ ጠቆመን።



አቶ በለው ልዑልሰገድ
በልዩ ሎተሪ-2
ብር 1,500,000
ድሬደዋ

ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ላይ አዳማ ስንደርስ እህል ቢጤ አፋችን ላይ አሟሸን። እንቅልፍ ተጫጭኖት የነበረው ካሜራ ማናችንም ነቃ ማለት ጀመረ። ጨዋታንና እንደግበዓት ተጠቅመን አስበ ተፈሪ ምሳ ለመብላት ወርድን።

መኪናችን ያየ አንድ ሰው ወደ እኛ መጣ። መኪናችን ላይ አንድ ባነር ተሰቅሏል። የተሰቀለው ባነር የዕድለኛውን ስም ያገኘውን የብር መጠን የሚገልጽ ነው፡፤ ስላምታ ካቀረብልን በኋላ -

‹‹ባንድ ቁጥር ብቻ  እኮ ነው ያመለጠኝ-››ድምፁ ላይ ቁጭት አለ

-‹‹ምኑ››  አልነው ባንድ ላይ

-‹‹ዕጣው ነዋ አንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር። ብታዩ የዚያ ቀን መተኛት አልቻልኩም። በዕድሌ በጣም ነው ያዘንኩት ---›› አለን ፤ሚያዝያ 28 ስለወጣው ልዩ ሎተሪ 2 መሆኑ ተገልፀልን።

‹‹የመጨረሻ ቁጥር ብቻ ነው የተለያየው ያንተ ›› ሲል  ጥያቄ አቀረበለት ካሜራ ማኑ

‹‹አዎ የኔ የመጨረሻው 8 ሲሆን የወጣው ግን  7 ነው››  በማለት ምላሽ ሰጠ

‹‹አይዞህ ሌላ ዕድል መሞከር ነው ››  አልነው

‹‹በእርግጥ አሁንም እኔም ተስፋ አልቆረጥኩም ፤ ይኸው ሌላ ቶምቦላ ገዝቻለሁ›› አለና ፣የገዛውን አንድ ሎተሪ አሳየን።

‹‹ግን አሁን ልትሸልሙት እየሄዳችሁ ነው?›› ፊቱ ላይ ያለማመን ስሜት ይታያል

‹‹አዎ››

በዚህ መሀል

ያዝዝነው ምግብ መጣ። እንዲበላ ጋብዝነው። አንድ ጉርሻ ጉርሶ መልካም መንገድ ተመኝቶልን ተለየን። እኛም ስለዕድል የተወያየን ምሳችንን በልተን ተነሳን።አንዲት ቁጥር የህይወት መዘውር ስትለውጥ ተመለከትን። ወደ መኪና ስንገባ አንዱ መጥቶ የደረሰው ዘመዱ እንደሆነ ነገረን። ምሳችንን እስከምንበላ ድረስ መኪናውን እየከበቡ ሳይነጋገሩ የሚያልፉ ማግኘት ተአምር ነው ቢባል ማጋነን አይደል። አድናቆታቸውን በጭንቅላታቸው እያወዛወዙ ይጓዛሉ። አስበተፈሪ ያገኘነው ታሪክ እየሰለቀጥን ደንገጎ ደረስን። ደንገጎ ጠመዝማዛና አደገኛ መንገድ ነው። የደንጎጎ ጠመዝማዝነት ለኔ ምን ያስየኝ የኑሮን ውጣ ውረድ ነው። ከዚህ ባሻገር የዕድል አዙሪት ነው። አዙሪቷ ዞራ ዞራ ድሬደዋ ደርሳለች። የመኪናችን ጎማ ሲሽከረከር የዕጣ ማሽኑ ሲሽከረከር አንድ ነው የሆነልኝ።

ድሬደዋ በሙቀት እኳን ደህና መጣችሁ አለችን። መንገዱ አድካሚ ቢሆንም ሁላችንም ድሬደዋ ስናይ መንፈሳችን ታደሰን። ድሬደዋ ነገ ለመጀመሪያ ጊዜ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ያዘጋጀውን ከፍተኛ የሎተሪ ዕድለኛ ልታይ ነው። እውነት ለመናገር ሙቀቷን አልቻልንም። በጣም ግላ ነበር የጠበቀችን።

ጠዋት ስንነሳ /1፡30/ ላይ ከረፈዱ አራት ሰዓት ይመስላል። እድለኞችንን ከድሬደዋ ቅርንጫፍ ለማግኘት ነጎደን። ከሱ ጋር ያደረግነው ቆይታ ያገኘነው ይህን ይመስላል።

ዕድለኛው አቶ በለው ሉዑል ሰገድ ይባላል። ተወልዶ ያደገው መርሳ ነው፤በንግዱ ዓለም እንዳለ እና አሁንም ነጋዴ እንደሆነ ገለፀልን። አቶ በለው ባገኘነው ጊዜ እንደ አደይ አባባ ፈክቶ ያገኘነው። ለምን አይፈነድቅ የ1.5 ሚሊዮን ብር ዕድለኛ አይደል!ዕድለኛችን የ1.5 ሚሊዮን ብር የምታስገኘውን ሎተሪ እንዴት እንደቆረጣት እንዲህ በማለት ገለፀልን። ‹‹ከጓደኞቼ ጋር ከምሸጥበት ሱቅ አብረን ተቀምጠን እየተጫወትን ሳለ ነው የቆረጥኩት››

የሁለት ልጆች አባት የሆነው አቶ በለው በደረሰው ገንዘብ በድሬደዋ ከተማ ኢንቨስት ለማድረግ እንዳቀደ ተናግሯል፡፡

‹‹ዕድለኛ መሆኔን እንዳወኩኝ መጀመሪያ  በጣም ለምውዳት እህቴ በስልክ ነገርኳት››ብሏል

አሁን 1.5 ሚሊዮን ደርሶዎታል ምን ተሰማዎት ስንለው ‹‹ምን ነካህ እንኳን 1.5 ሚሊዮን ብር ብቻ አይደለም የጣልከው ዕቁብ እንኳን ሲደርስህ በጣም ነው ደስ የሚለው የእኔም ደስታ ወደር የለውም›› ሲል ምላሽ ሰጥቶናል፡፡

ረፋዱ ላይ የሽልማቱ ስነ ስርዓት ተጠናቀቀ፡፡ በእውነት እዚያ አካባቢ የነበረው ደስታ ልዩ ነበር፡፡ ደስታውንም የዛሬው ልዩ  ቀን

ቢደገም ቀን በቀን

ሲል አቀንቅኗል፡፡ ለነገሩ የደረሰው ልዩ ሎተሪ ነበር፡፡